፻፷፪ ናጥሪ እንከ አፍቅሮ ወየ ዋሃተ ከመ ሐዋርያት እስመ አፍቀርዎ ለእግ ዚአሙ ዘወሀቦሙ ሥል ጣነ ዘከማሁ ይዕሥሩ ወይፍትሑ ኵሎ ማዕ ሠረ ዐመፃ ።	፻፷፪ እንግዲህ እንደ ሐዋር ያት ፍቅርን የዋሃት ንም ገንዘብ እናድርግ ፣ ጌታቸውን ወደውታልና ፣ የዓመፃ ማሠሪያን ሁሉ ያሥሩ ይፈቱም ዘንድ እንደርሱ ያለ ሥልጣንን የሰጣቸው ።	162. Let us henceforth have love and meekness like the apostles, because they loved their Lord who granted them authority like His own to bind and loose the bonds of wickedness.
፻፷፫ ናጥሪ እንከ አርምሞ ወትዕግሥተ ከመ ማር ያም እስመ ወደሳ እግ ዚእነ እንዘ ይብል ማርያምሰ ኀርየት መክ ፈልተ ሠናየ ዘኢየኀ ይድዋ ።	፻፷፫ እንግዲህ እንደ ማር ያም አርምሞንና ትዕግ ሥትን ገንዘብ እናድርግ ፣ ማርያምስ የማይቀምዋት በጎ እድልን መረጠች ብሎ ጌታችን አመሰግኗ ታልና ።	163. Let us henceforth have silence and patience like Mary because our Lord praised her saying: And Mary hath chosen that good part, which shall not be taken away from her.[38]
፻፷፬ ወይእዜኒ ንስአሎ ለጸ ጋዌ ጸጋ እግዚአብሔር አምላክነ ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ ።	፻፷፬ አሁንም ጸጋን የሰጠ አምላካችንን እግዚአብ ሔርን እንለምነው ። ይ.ዲ. ጸልዩ ።	164. And now let us pray the Lord our God, giver of grace. *Deacon*: You pray.
፻፷፭ ይ. ካ. ኦ ድንግል አዘ ክሪ ኀበ መዘክር ዘኢይ ረስዕ ኵሎ ።	፻፷፭ ይ.ካ. ድንግል ሆይ ከሚያስብ ሁሉን ከማ ይዘነጋ ከልጅሽ ዘንድ አሳስቢ ።	165. *Priest*: O Virgin, remind Him who remembers, who never forget any.
፻፷፮ አዘክሪ ድንግል ልደቶ እምኔኪ ዘተወልደ በቤተ ልሔም ወዘተጠብለለ በአፅርቅት ወአስተማወ ቅዎ እስትንፋሰ አድግ ወላሕም በመዋዕለ ቍር ።	፻፷፮ ድንግል ሆይ ፣ በቤተ ልሔም ካንቺ የተወ ለደውን መወለድ ፣ በጨርቅ የተጠቀለለው ንም አድኅኖ (አህያና) ላም በብርድ ወራት እስትንፋስን ያሟሟቁ ትንም አሳስቢ ።	166. O Virgin, remind him of His birth, delivered from you at Bethlehem, of His being wrapped in swaddling clothes and His being warmed by the breath of ass and cow on the cold days.

[38] Luke 10:42.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፪፻፶፯፤ አዘክሪ ድንግል ንግደቶ ዘምስሌኪ እንዘ ትጉ ይዩ ምስሌሁ እም ሀገር ለሀገር በመዋዕለ ሄሮድስ ርጉም፤	፪፻፶፯፤ ድንግል ሆይ ፣ ርጉም በሆነ በሄሮድስ ዘመን ከርሱ ከአገር ወደ አገር ስትሸሺ ካንቺ ጋራ መሰደዱን አሳስቢ፤	167. O Virgin, remind Him of his flight with you when you did travel from one country to another in the days of the cursed Herod.
፪፻፶፰፤ አዘክሪ ድንግል አንብዐ መሪረ ዘውኅዘ እም አዕይንትኪ ወወረደ ዲበ ገጸ ፍቁር ወልድኪ፤	፪፻፶፰፤ ድንግል ሆይ፤ ከዓይኖ ችሽ የፈሰሰውንና በተወ ደደ ልጅሽ ፊት የወረ ደውን መሪር እንባ አሳስቢ ፤	168. O Virgin, remind Him of the bitter tears shed from your eyes and dropped on the face of your beloved Son.
፪፻፶፱፤ አዘክሪ ድንግል ረኀበ ወጽምዓ ምንዳቤ ወኀዘነ ወኵሉ አጸባ ዘበጽሐኪ ምስሌሁ፤	፪፻፶፱፤ ድንግል ሆይ ረኃቡንና ጥሙን ችግሩንና ኃዘኑን ከርሱ ጋራ የደረሰብሽ ንም ጭንቀት ሁሉ አሳስቢ፤	169. O Virgin, remind Him of hunger, thirst, poverty, sadness and all the trouble which you did suffer together with Him.
፪፻፷፤ አዘክሪ ሣህለ ወአኮ ተጋ ጕሎ፤ አዘክሪ ምሕረተ ወአኮ መዓተ፤	፪፻፷፤ ጥፋትን ያይደለ ይቅር ታን አሳስቢ፤ መዓትን ያይደለ ምሕረትን አሳ ስቢ፤	170. Remind Him of mercy and not of destruction. Remind Him of compassion and not of anger.
፪፻፷፩፤ አዘክሪ ለኃጥኣን ወአኮ ለጻድቃን፤ አዘክሪ ለርሱ ሓን ወአኮ ለንጹሓን፤	፪፻፷፩፤ ለጻድቃን ያይደለ ለኃጥ አን አሳስቢ፤ ለንጹሐን ያይደለ ለተጻደፉት አሳ ስቢ ፤	171. Remind Him of the sinners and not of the righteous. Remind Him of the impure and not of the pure.
፪፻፷፪፤ ወይእዜኒ ንስብሖ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘል ፈኒ ወለ ዓለመ ዓለም፤ ይ . ሕ. ፤ አሜን ፤	፪፻፷፪፤ አሁንም አብንና ወል ድን መንፈስ ቅዱስንም እናመስግነው ለዘለ ዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፤	172. And now let us glorify the Father, the Son and the Holy Spirit, both now and ever, and world without end. *People*: Amen.
፪፻፷፫፤ ይ. ካ. አንብሮ እድ፤ ነአኵቶ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ጸጋ ዘወ ሀባ ወአሠልጠና ለእመ በላዕለ ዛቲ ቅዳሴ፤ ወለነኒ ዘረሰየነ ድልዋነ ንንብብ በኒሩቱ ወንፈጽም በሥምረቱ ዘሎቱ ስብ ሐት ወውእቱ ጠቢብ ለዓለመ ዓለም አሜን ፤	፪፻፷፫፤ ይ.ካ. አንብሮ እድ፤ ለእናቱ ስለ ሰጣት ጸጋ ሁሉ በዚህችም ቅዳሴ ላይ ስለ አሠለጠናት እግዚአብሔርን እናመሰ ግነዋለን ፤ እኛንም በቸ ርነቱ እንናገር ዘንድ በፈቃዱም እንፈጽም ዘንድ የተዘጋጀን ያደረ ገን ፤ ምስጋና ያለው እርሱ ነው፤ ጥበበኛም ነው፤ ለዘለዓለሙ አሜን፤	173. *Priest*: *The Laying on of the Hand.* We offer thanksgiving to God for all the graces he has granted and because He granted his Mother to be glorified through this Anaphora, and because He made us worthy to begin it through His kindness, and to complete it through His will, He too whom is glory and who is wise, world without end, Amen.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፪፻፸፬፤ ይ. ካ. ወረከብኩ በውስ ቴታ ዘይብል ዘንተ ቅዳሴ ዘይቄድስ ካህን አኮ ማርያምሃ ዘይቄድስ አላ ውእቱ ይትቄደስ ወእለ ሰምዕም ኵሎሙ ይት ቄደሱ፤ እስመ እግዝእ ትነሰ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወትረ በሰማይ ወበምድር፤	፪፻፸፬፤ ይ. ካ. በውስጥዋ ይህን ቅዳሴ የሚቀድስ ካህን ማርያምን የሚቀድስ አይደለም የሚል አገኘሁ እርሱ ይቀደሳል እንጂ፣ የሰሙትም ሁሉ ይከብ ራሉ፤ እመቤታችን ማር ያም ግን በሰማይና በምድር ዘወትር የተ መሰገነች ናትና፤	174. (I found in it that which says. Any priest who celebrates this Anaphora does not sanctify Mary but he himself will be sanctified, and all those who hear it will be sanctified, because our Lady Mary is always sanctified in heaven and earth.)
፪፻፸፭፤ በረከተ ጸሎታ ውኩፍ ወሀብተ ረድኤታ ትሩፍ ወምሕረተ ፍቁር ወልዳ ምልዕተ አጽናፍ የሃሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን።	፪፻፸፭፤ የሚቀበለው የልመናዋ ክብር ፍጹም የሆነ የረድኤትዋ ሀብት ጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚሞላ፣ የተወደደ የልጅዋ ቸር ኑት በእውነት ከሁላችን ጋራ ይሁን፣ ለዘለ ዓለሙ አሜን ።	175. May the accepted blessing of her prayer, tbe perfect gift of her help, and the compassion of her beloved Son, filling the ends (of the world), be with all of us world without end. Amen.
* * *	* * *	* * *

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምእት ጸሎተ ሃይማኖት ፤	**የሠለስቱ ምእት ቅዳሴ** የሃይማኖት ጸሎት ፤	**THE ANAPHORA OF THE THREE HUNDRED** [1] ***The Prayer of the Faith .*** [2] ***(Creed)***
፩ ፤ ነአምን በ፩ዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወም ድር ዘያስተርኢ ወዘኢያ ስተርኢ ፤	፩ ፤ ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን ፤ የሚታይና የማ ይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ፤	**1. We believe in one God the Father almighty, maker of heaven, earth and all things visible and invisible.**
፪ ፤ ወነአምን በ፩ዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው ምስ ሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ፤	፪ ፤ ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋራ በነበረ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እና ምናለን ፤	**2. And we believe in one Lord Jesus Christ, the only-begotten Son of the Father who was with him before the creation of the world:**
፫ ፤ ብርሃን ዘእምብርሃን አም ላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመ ለኮቱ ፤	፫ ፤ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፤ ከእውነተኛ አምላክ የተ ገኘ አምላክ ፤ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ ፤ በመለ ኮቱ ከአብ ጋራ የሚተ ካከል ፤	**3. Light from light, true God from true God, begotten not made, of one essence with the Father.**
፬ ፤ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበ ሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢ ምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘ በምድርኒ ፤	፬ ፤ ሁሉ በርሱ የሆነ ፤ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም ፤ በሰማይም ያለ በምድርም ያለ ፤	**4. By whom all things were made, and without him was not anything in heaven or earth made:**
፭ ፤ ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበ እንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ፤ ተሰብአ ወተ ሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ፤	፭ ፤ ስለ እኛ ስለ ሰው ስለ መዳናችን ከሰማይ ወረደ ፤ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ከቅድስት ድንግል ማር ያምም ፈጽሞ ሰው ሆነ ፤	**5. Who for us men and for our salvation came down from heaven, was made man and was incarnate from the Holy Spirit and from the holy Virgin Mary.**
፮ ፤ ኮነ ብእሴ ወተሰቅለ በእን ቲአነ ፤ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጠናዊ ፤ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ፤	፮ ፤ ሰው ሁኖ በጰንጠናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረም ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ በቅዱሳት መጻሕ ፍት እንደ ተጻፈ ፤	**6. Became man, was crucified for our sakes in the days of Pontius Pilate, suffered, died, was buried and rose from the dead on the third day as was written in the holy scrip-tures:**

[1] When the 318 bishops, members of the first ecumenical Council held at Nicea in 325 A.D., settled the questions under discussion, they wrote some literature, among which was this Anaphora.
It is celebrated on the following occasions.

a) On 21st Maskaram (Tout – September), the memorial day of the Virgin Mary.
b) On 8th Hedar (Hatour- November), the Feast of the Four Beasts.
c) On 9th Hedar (Hatour – November), the opening day of the Council of Nicea.
d) On 24th Hedar (Hatour – November), the Feast of the Twentyfour heavenly Priests.
e) On Christmas.
f) On 13th Ter (Touba – January), the Feast of Cana of Galilee.
g) On the memorial day of any of the righteous.

[2] The creed given by the Council of Nicea and the Council of Constantinople.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፯፤ ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ፤ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወመ·ታነ፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፤	፯፤ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛ ሕያዋንን መ·ታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፤	7. Ascended in glory into heaven, sat at the right hand of his Father, and will come again in glory to judge the living and the dead; there is no end of his reign.
፰፤ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወ ልድ ዘነበበ በነቢያት፤	፰፤ ጌታ ማሕየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፤ እን ሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋራ በነቢያት የተናገረ ፤	8. And we believe in the Holy Spirit,[3] the life-giving God, who proceeds from the Father; we worship and glorify him with the Father and the Son; who spoke by the prophets,
፱፤ ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ገባኤ ዘሐዋ ርያት፤	፱፤ ከሁሉ በላይ በምትሆን፤ ሐዋርያት በሰበሰብዋት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን፤	9. and we believe in one holy, universal, apostolic Church,
፲፤ ወነአምን በአሐቲ ጥም ቀት ለሥርየተ ኃጢአት፤ ወንሴፎ ትንሣኤ መ·ታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም፤	፲፤ ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናም ናለን፤ የመ·ታንንም መነ ሣት ተስፋ እናደርጋለን፤ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለመ·፤	10. and we believe in one baptism for the remission of sins, and wait for the resurrection from the dead and the life to come, world without end. Amen.
* * *	* * *	* * *
፲፩፤ አኰቴተ ቍርባን ዘሠለስቱ ምእት ፫፻፲፰ውያን ርቱዓነ ሃይማኖት ጸሎ ቶሙ· ወበረከቶሙ· የሃሉ ምስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቲነ አባ ዕገሌ ወምስለ ሊቀ ጳጳስነ አባ ዕገሌ ወምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ወዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ለዓለመ ዓለም አሜን፤	፲፩፤ ሃይማኖታቸው የቀና ፫፻፲፰ኛ ሊቃውንት የተናገሩት የቁርባን ምስጋና ጸሎ ታቸውና በረከታቸው ከጳጳሳቱ አለቃ አባ ዕገሌና ከጳጳሳችን አባ ዕገሌ ከሁላችንም ጋራ ይሁን፤ አገራችን ኢትዮ ጵያንም ይጠብቃት ፤ ለዘለዓለመ· አሜን ፤	11. The Anaphora of the Three Hundred and eighteen orthodox scholars; may their prayers and their blessings be with our patriarch ... archbishop ... with all Christians and with our country Ethiopia world without end. Amen.
፲፪፤ ይካ. እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ· ፤ ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ ፤ ይ. ካ. አእኵትዎ ለአም ላክነ፤ ይ. ሕ. ርቱዕ ይደሉ፤ ይ. ካ. አልዕሉ አልባቢ ክሙ·፤ ይ. ሕ. ብነ ኀበ እግዚ አብሔር አምላክነ፤	፲፪፤ ይካ. እግዚአብሔር ከሁ ላችሁ ጋራ ይሁን ፤ ይ.ሕ. ከመንፈስህ ጋራ፤ ይ.ካ. አምላካችንን አመ ስግኑት ፤ ይ.ሕ. እውነት ነው ይገባል ፤ ይ.ካ. ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ ፤ ይ.ሕ. በአምላካችን በእግ ዚአብሔር ዘንድ አለን፤	12. *Priest*: The Lord be with you all. *People*: And with your spirit. *Priest*: You Give thanks unto our God, *People*: It is right, it is just. *Priest*: Lift up your hearts. *People*: We have lifted them up unto the Lord our God.

[3] This is the end of the Nicene Creed. What follows was given by the Second Council held in Constantinople

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፲፫፤ ይ. ካ. ግሩም በውስተ ደመናት ወልዑል እምሰ ማያት፤ እግዚአብሔር ስቡሕ በኵሉ ፍናዊሁ አምላክ አማልክት ፀባ ያት ፍጹም፤	፲፫፤ ይ.ካ. በደመናት ግሩም ነው፤ ከሰማያትም ይልቅ ከፍ ያለ ነው፤ እግዚ. አብሔር በመንገዱ ሁሉ ምስጉን ነው፤ የአማል ክት አምላክ ፍጹም አሸ ናፊ ነው ፤	13. *Priest*: The Lord is mighty in the clouds, higher than heaven, glorious in all his ways, the perfect victorious God of gods.
፲፬፤ አልቦ አመ ኢሀሎ ወአ ልቦ አመ ተነጥአ ወአ ልቦ አመ አስተርአየ ፍጹመ በመለኮቱ፤ አልቦ ዘይክል ርእዮቶ ወአልቦ ዘየአምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ ፤	፲፬፤ የሌለበት ጊዜ የለም፤ የታጣበትም ጊዜ የለም፤ በመለኮቱ ግን ፈጽሞ የታየበት ጊዜ የለም፤ እርሱን ማየት የሚችል የለም፤ አነዋወሩም እን ደምን እንደሆነ የሚያውቅ የለም ፤	14. There is no time in which He was not, and there is no place where He cannot be found, there is no time when He was perfectly seen in His divinity. No one can see Him, and no one knows how He lives.
፲፭፤ ዘኪያሁ ይሴብሑ ሰማ ያት ወምድር ምስለ ኵሉ ዓለሙ ባሕር ወአፍላግ ወኵሉ ዘውስቴቶሙ፤ ዘበጸጋሁ ተፈጥረ ኵሉ ወበኂሩቱ ይበይት ኵሉ፤ ዘውእቱ ዋሕድ አበ ዋሕድ አበ እግዚእ አበ መሢሕ ዘበአማን ብርሃን ምስለ ዘወለዶ፤	፲፭፤ ሰማይና ምድር ከዓለማ ቸው ሁሉ ጋራ ባሕርና ወንዞች በውስጣቸውም ያሉ ሁሉ እርሱን የሚያ መሰግኑ፤ በጸጋው ሁሉ የተፈጠረ በቸርነቱም ሁሉ የሚያድር፤ ይኸ ውም አንድ የሚሆን ያንድ አባት፤ የጌታ አባት ከወለደው ጋራ እውነተኛ ብርሃን የሚሆን የመሢሕ አባት ነው፤	15. Heaven and earth together with all their worlds, sea and rivers and all things that are in them glorify Him. All were created through His grace, and all live through His kindness. He is one Father of the One, Father of the Lord, Father of Messiah, true light with Him who begat Him.
፲፮፤ ይ. ዲ. አውሥኡ፤ ይ. ሕ. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባያት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐ ቲከ፤	፲፮፤ ይዲ. ተሰጥዎውን መልሱ፤ ይ.ሕ. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በም ድር የመላ ነው ፤	16. *Deacon*: You answer. *People*: Holy holy holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the holiness of your glory.
፲፯፤ ይ. ካ. ንዜኑ ህላዌሁ ለአብ ምስለ ወልዱ ወህ ላዌሁ ለወልድ ምስለ አቡሁ፤ እምቅድመ ኵሉ ፍጥረት፤ ወእምቅድመ ግብረተ ሰማያት፤ እም ቅድመ ትሣረር ምድር፤	፲፯፤ ይ.ካ. የአብን ክልጁ ጋራ አነዋወሩን የወልድንም ከአባቱ ጋራ አነዋወሩን እንናገራለን ከፍጥረት ሁሉ በፊት ፤ ከሰማያ ትም መፈጠር በፊት፤ ምድር ሳትፈጠር፤	17. *Priest*: We Proclaim that the Father lived with His Son, and that the Son lived with His Father before creation, and before the heavens and earth were made:
፲፰፤ ወእምቅድመ ይቁሙ አድ ባር ወአውግር፤ ወእምቅ ድመ ያስተርኢ ኑኅ አየር፤ ወእምቅድመ ይንፋሕ ኃይለ ነፋስ፤	፲፰፤ ተራራዎችና ኮረብቶች ሳይቆሙ፤ የአየርም ርዝ መት ሳይታይ ፤ የነፋስ ኃይል ሳይነፍስ ፤	18. and before the mountains and the little hills arose, and before the height of the sky was seen, and before the power of the wind breathed,
፲፱፤ ወእምቅድመ ያንበስብስ ፀዓዕ፤ ወእምቅድመ ያስ ተርኢ ብልሐተ መብረቅ፤ ወእምቅድመ ይድምፅ ነጐድጓድ ወይሰፍሑ ደመናት፤	፲፱፤ ብልጭልጭታም ሳይመላ ለስ፤ የመብረቅም ፍጥ ነት ሳይታይ፤ ነጐድጓድም ሳይሰማ፤ ደመናትም ሳይ ዘረጉ፤	19. and before the thunder-bolt flashed, and before the quickness of light-ening was seen, and before the thunder thundered, and before the clouds were spread,

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፳፤ ወእምቅድመ ፍጥረተ መላእክት፤ እምቅድመ ኵሉ ስም ዘይሰመይ በ ታ ሕ ተ ሰ ማ ይ ወምድር፤	፳፤ ከመላእክትም መፈጠር በፊት ከሰማይ በታች ከምድርም ከሚጠራ ስም ሁሉ በፊት፤	20. and before the creation of angels, and before any name was named under heaven and on earth.
፳፩፤ ወኢመኑሂ ሐሊዮ ወአዕሚቆ ኢይክል ረኪበ ህላዌሁ እመሂ ተለዐለ እስከ ሰማያት ወጎለፈ እምኀበ አጋዕዝት፤ ወረከበ ፬ተ እንስሳ ምሉዓነ አዕይንት ዘኵለንታሆሙ ፀዳል ወእምአፉሆሙ ይወፅእ አምሳለ ነደ እሳት፤ ወካዕበ ለእመ ወረደ ምድረ ወጎለፈ ባሕረ ነፋሰ ወእሳተ፤ ወካዕበ ለእመ ወፅአ እምህየ ወጎሠሠ የማነ ወፀጋመ ኢበምክሕ ወኢ በጸቢተ ሕሊና፤	፳፩፤ ማንም አስቦ አጥልቆም አነዋወሩን ማግኘት አይችልም ፤ ምንም እስከ ሰማይ ቢወጣ ከአጋዕዝትም ዘንድ ቢያልፍ፤ ዓይንን የተመሉ ፤ ሁለንተናቸው ብርሃን የሚሆን፤ ከአን ደበታቸው ነደ እሳት የሚመስል ቅዳሴ የሚወጣ አራቱ እንስሳንም ቢያገኝ፤ ዳግመኛም ወደ ምድር ቢወርድ ባሕር ንና ነፋስን እሳትንም አልፎ ቢሄድ ፤ ዳግመኛም ከዚያ ወጥቶ በመ መካትም ሆኖ በሕሊናም በመዋኘት ቀኙንና ግራ ውን ቢመረምር ፤	21. No one, thinking deeply, can understand His nature, though He ascends to heaven and goes beyond the lords and meets with the four living creatures,[4] full of eyes, whose whole bodies are light, and from whose mouths comes out the likeness of flaming fire; again, though he descends down to earth and goes beyond the sea, the wind and the fire; again, though he goes out thence to search upon the right hand and the left, setting his thought on high and spreading it abroad:
፳፪፤ ይ. ዲ. እለ ትነብሩ ተንሥኡ፤	፳፪፤ ይ.ዲ. የተቀመጣችሁ ተነሡ፤	22. *Deacon*: You that are sitting, stand up.
፳፫፤ ይ. ካ. ኢይክል ይባእ ማዕከለ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከመ ያእምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ፤	፳፫፤ ይ.ካ. አነዋወሩ እንዴት እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ በአብና በወልድ በመን ፈስ ቅዱስም መካከል ሊገባ አይችልም ፤	23. *Priest*: Even so He cannot discern among the Father, the Son and the Holy Spirit to know what His nature is.
፳፬፤ ወለዶ አብ ለወልዱ ኢይ ትበሃል ዘ ጊዜ ወበዘ ከመዝ መዋዕል ወለዶ፤	፳፬፤ አብ ልጁን ወለደው ፤ በዚህ ጊዜ ፤ እንዲህ ባለ ዘመንም ወለደው አይባልም ፤	24. The Father begat his Son, but it is impossible to say that He begat Him at such a time or that He begat Him on such and such a day.
፳፭፤ ኢይትአመር ልደቱ እም አብ እስመ ዕፁብ ውእቱ ወኢይትዐወቅ ህላዌሁ እስመ ሥውር ውእቱ ፤ ውእቱ ለአቡሁ የማኑ እደ መዝራዕቱ ወልዱ ወፍቁሩ ዘከማሁ አምሳሊሁ፤	፳፭፤ ከአብ መወለዱ አይታ ወቅም፤ ጭንቅ ነውና፤ አነዋወሩም ይታወቅም፤ የተሠወረ ነውና፤ ለአባቱ ቀኙ ነው፤ ክንዱ ልጁ ወዳጁም፤ እንደርሱ የሚ ሆን የሚመስለው ነው፤	25. His birth from the Father is unsearchable because it passes understanding, and His nature is unknown because it is hidden. He is the right hand of His Father, His arm and his beloved Son who is of the same essence with him.
፳፮፤ ይ. ዲ. ውስተ ጽባሕ ነጽሩ ።	፳፮፤ ይ.ዲ. ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ ።	26. *Deacon*: Look to the east.
* * *	* * *	* * *

[4] Ezek. 1.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፳፯፤ ይ. ካ. ወለዶ አብ ለወልዱ፤ አኮ በምክንያት ዘወለዶ ለመርድኦ ግብር ከመ ይትለአኮ ዘከመ ተፀነሰ፤ ወአመ ፈጠረ ሰማያተ ወምድረ አልቦ ዘረድኦ እስመ ከሃሊ ውእቱ፤	፳፯፤ ይ.ካ. አብ ልጁን ወለደው፤ እንደ ተቸገረ ሰው ያገለግለው ዘንድ ሊሠራ እርዳታ በምክንያት የወለደው አይደለም፤ ሰማይንና ምድርን በፈጠረም ጊዜ የረዳው የለም፤ ከሃሊ ነውና ፤	27. *Priest*: The Father begat His Son; but He did not beget Him that He might be His assistant in work to serve Him as a man is served who is in difficulty. When He created heaven and earth no one helped Him because He is mighty.
፳፰፤ አኮ ከመ ብእሲ ዘደክመ ወፃመወ ወአዕረፈ አላ ሰይፈ አሳት ይወፅእ እምአፉሁ ዘነበበ በጊዜሃ ይገብሮ ወዘሐለየ በቅጽበት ይከውኖ ዘውእቱ ሕሊና ሕሊናት ጠቢብ ወኬንያ ፤	፳፰፤ እንደ ሰው ደክሞት ያረፈ አይደለም፤ የእሳት ሰይፍ ከአፉ ይወጣል እንጂ፤ የተናገረውን በዚያው ጊዜ ያደርጋል፤ ያሰበውም በቅጽበት ይሆንለታል፤ የሕሊናት ሕሊና ጥበበኛም ብልሃተኛም እርሱ ነው ፤	28. He did not become weary, nor did He rest as a man rests, but the sword of fire coming out of His mouth, what He has spoken is immediately accomplished; in a moment what He has thought is fulfilled: He is the thought of thoughts;[5] He is the Wise, the Maker.
፳፱፤ መኑ ኮማሁ ይጼዐን ቀመረ ወየሐንፅ መሠረተ ይፀ ውር ድደ ወ ይነ ብ ር ጠፈረ፤ ይሣርር ዲበ ማይ ወ የ ሐ ን ፅ በደቃቅ ወይጠበልል በረቂቅ፤ ይቄስን በኖግ ወይ ፄምድ በነፋስ ይሰቅል ማየ ወይሰሚ ሰማየ፤	፳፱፤ እንደርሱ በቀመር የሚቀ መጥ፤ መሠረትን የሚ ሠራ፤ መሠረትን ተሸክሞ በጠፈር የሚኖር ማነው? በውኃ ላይ ይመሠርታል በጥቃቅን ይሠራል፤ በረ ቂቅ ይጠቀልላል፤ በአ ሸዋ ይወስናል፤ በነፋስ ያጸናል፤ ውኃውን ሰቅሎ ሰማይ ይለዋል ፤	29. Who, like him, lives in the highest heaven,[6] builds the foundation, bears up from beneath, sits upon the firmament on high, establishes upon the floods, builds with very small particles, wrapps with invisible things, limits with sand, strengthens with wind, hangs the water up and calls it sky,
፴፤ የዐቍር ማየ በማኅፀን ወያረግፅ ከመ ይኩን ሥጋ የዐሥር በአሥራው ወያ ጸንዕ በአምትንት ይኋ ልቍ አሥዕርተ፤ ይፈ ትን ልበ ወየአምር ኵል ያተ ፤	፴፤ ውኃን በማኅፀን ይቋጥ ራል፤ ሥጋም ይሆን ዘንድ ያረጋዋል፤ በሥር ያሥረዋል፤ በጅማትም ያጸናዋል፤ ጠጕርን ይቁ ጥራል ፤ ልብን ይመረ ምራል ኵላሊትንም ያው ቃል፤	30. curdls water in the womb, turning it into flesh, binds it with muscles, strengthening it with sinews, numbers the very hairs, tries the heart and knows the reins?
፴፩፤ ወለዶ አብ ለወልዱ አልቦ ዕለት ወአልቦ ሰዓት፤ ወአመ ወለዶ ኢተባሕ ተወ አቡሁ ሎቱ፤ እም ቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ስብሐቲሁ ዘተፀርዐ አላ ምሉዕ ውእቱ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤	፴፩፤ አብ ልጁን ወለደው፤ ዕለት ግን የለም፤ ሰዓትም የለም፤ በወለደ ውም ጊዜ አባቱ ከርሱ ብቸኛ አልሆነም፤ መላ እክትንም ለምስጋና ሳይ ፈጥር ምስጋናው የተቋ ረጠ አይደለም፤ የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ምስጋና የመላ ነው እንጂ ፤	31. The Father begat His Son without days or hours; and when He begat him His Father was not separated from Him. Before He created the angels for His worship His glory was infinite; the glory of the Father, of the Son and of the Holy Spirit was perfect.

[5] i.e. he knows the thoughts of all, but his thought can be known by none.
[6] i.e. the foundation of the earth.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፴፪፤ ይ. ዲ. ንነጽር ፤	፴፪፤ ይ.ዲ. እናስተውል ፤	32. *Deacon*: Let us give heed.
፴፫፤ ይ. ካ. ወአመ ፈጠሮ ለአቡነ አዳም አኮ ዘእን ሶሰወ ከመ ያምጽእ መሬተ ወማየ ነፋሰ ወእሳተ፤ አላ እመንበሩ ኢተሐውሰ ወኢያንቀልቀለ ፍጹመ ፤	፴፫፤ ይ.ካ. አባታችንን አዳምን በፈጠረውም ጊዜ መሬት ንና ውኃን ነፋስንና እሳ ትን ያመጣ ዘንድ የተመ ላለሰ አይደለም፤ ከዙፋኑ ሳይነቃነቅ ፈጽሞ ሳይነ ዋወጥም ነው እንጂ፤	33. *Priest*: And when he created our Father Adam He did not go about to bring earth, water, wind and fire; and did not leave his throne or in any way move from it:
፴፬፤ ወእንዘ ሀሎ ህየ ነሥአ ፬ተ ጠባይዐ ፪ተ እምዘ ይትገሠሥ ወ፪ተ እምዘ ኢይትገሠሥ ፫ተ እም ዘይትረአይ ወ፩ደ እም ዘኢይትረአይ ፤	፴፬፤ በዚያም ሳለ አራቱን ባሕርያት ነሣ፤ ሁለቱን ከሚዳሰስ ሁለቱን ግን ከማይዳሰስ፤ ሦስቱን ከሚ ታይ አንዱን ከማይታይ፤	34. Yes, while He was yet there He took the four elements, two palpable and two impalpable; three visible and one invisible;
፴፭፤ ቦቱ ለሐኮ ወአሠነዮ በእ ደዊሁ ቅዱሳት ሰዐሞ ወአፍቀሮ፤ ወነፍሐ ላዕ ሌሁ መንፈሰ ሕይወት እምቅድመ ይሕንፅ አየ ራተ ወአርያማተ አኮ ዘተ ትሕተ አላ ጽኑዐ መንበር ወእዙዘ መንግሥት፤	፴፭፤ ቅዱሳት በሚሆኑ እጆቹ በርሱ አሳምሮ ፈጠረው ሳመው ወደደውም ፤ የሕይወትንም መንፈስ በርሱ ላይ እፍ አለ ፤ አየራትንና ሰማያትንም ሳይፈጥር የተዋረደ አይ ደለም፤ በዙፋን የጸና፤ በመንግሥትም የጸና ነው እንጂ ፤	35. And made him from these, made him fair with his holy hands, kissed him and loved him; and breathed in his nostrils the breath of life. Before He built the skies and the highest heavens He was not lowly, but was strong in His throne and great in His kingdom.
* * *	* * *	* * *
፴፮፤ ዘበላዕሉ አንጐድጐደ ወዘበታሕቱ አርዐደ ወደ መናተ ኬደ ዘእንበለ እሳት አንደደ ወዘእንበለ ማይ አብረደ፤	፴፮፤ በላይ ላሉት ድምፅን አሰማ፤ በታች ያሉት ንም አንቀጠቀጠ፤ ደመ ናትንም፤ ረገጠ፤ ያለ እሳት አቃጠለ ያለ ውኃም አቀዘቀዘ ፤	36. He thundered to those that were above, and caused to tremble those that were beneath; He trod the clouds, burned without fire and cooled without water.
፴፯፤ ወአመ ፈጠረ ፀሐየ ወወርኀ አኮ ከመ ያብ ርሁ ሎቱ ከመ ዘጸልሞ አላ ጸገሙ ንስቲተ እምዘዚአሁ ብርሃን መጠነ ኅጠተ ሥርናይ፤ ወበእን ተዝ አብርሁ ዲበ ሰብእ፤	፴፯፤ ፀሐይንና ጨረቃን በፈጠ ረም ጊዜ እንደ ጨለ መበት ሰው ሊያበሩለት አይደለም፤ ከርሱ ብር ሃን የስንዴ ቅንጣት ያህል ጥቂት ሰጣቸው እንጂ ፤ ስለዚህም በሰው ላይ አበሩ ፤	37. And when He created the sun and the moon it was not to give light to Him as to one in darkness but He gave them from his own light a little, as it were no more than a grain of wheat. Thus, they gave light to man.
፴፰፤ ወኮሎ እንከ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ፈጢሮ ወአስተናበሮ አኮ ዘተ መክሐ እንዘ ይብል ገበ ርኩ ወፈጸምኩ ወአ ዐርፍ እምነ ኵሉ ፃማ ዘረከበኒ፤ ውእቱሰ እም ቅድመ ይኩን አእመረ ወእምቅድመ ይግበር ፈጸመ እምቅድመ ይፍ ጥር (ይግበር) ጻድቃነ ወኃጥኣነ ሠናያነ ወእ ኩያነ፤	፴፰፤ እንግዲህ የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ ፈጥሮ አዘጋጅቶ ሠርቼ ፈጸምሁ ካገኘኝም ድካም ሁሉ አርፋለሁ ብሎ የተመካ አይደለም፤ እርሱ ሳይ ደረግ ዐወቀ ሳይሠራም ፈጸመ፤ ጻድቃንንና ኃጥ አንን ክፉምችንና በጎም ችን ሳይፈጥር ፤	38. Having created and prepared all, visible invisible, He did not boast saying, I have worked and I have finished and I have to rest from all the toil in which I have laboured; but He knew before it came to pass, He completed before ever He made righteous and unrighteous, good and evil.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፴፱፤ እምቅድመ ይፍጥሮ ለዕጓለ እመሕያው ገነተ አስተዳለወ ከመ ያብእ ውስቴታ ለዘአፍቀረ ወእሳተ ሲኦል አስተዳለወ ከመ ያብእ ውስቴታ ለዘጸልዐ፤	፴፱፤ ሰውን ሳይፈጥረው ገነ ትን አዘጋጀ፤ የወደደ ውን ወደ እርስዋ ያገባ ዘንድ፤ የሲኦልንም እሳት አዘጋጀ የጠላውን ወደ እርስዋ ያገባ ዘንድ ፤	39. Before He created man He prepared Paradise to put there Him whom He loved, and the fire of hell to put there him whom he hated.
፵፤ ብፁዕ ዘኀረዮ ወብፁዕ ዘአፍቀሮ ወብፁዕ ዘሠ ምሮ ኀለቡ እንከ ዘንተ ቃለ በዐቢይ ጥንቃቄ፤ ከመኢንባእ ውስተ ዐቢይ ባሕር ኀበ ተደመረ እሳት ወማይ ወኀበ ኢንክል ጸቢተ ወወሚአ እምኔሁ፤	፵፤ የመረጠው ብፁዕ ነው የወደደውም ብፁዕ ነው፤ እንግዲህ ይህን ቃል በፍጹም መጠንቀቅ እናስ ተውል፤ እሳትና ውኃ ወደተቀላቀለበት ከርሱም ዋኝቶ መውጣት ወደ ማይቻለን ታላቅ ባሕር እንዳንገባ ፤	40. Blessed is he whom he had chosen, and blessed is he in whom he was pleased. Let us therefore receive this word with great diligence that we may not enter into the great sea wherein fire and water are mingled and from which we can not escape by swimming.
፵፩፤ ንሕነሰ ኀለቡ በከመ መሐሩነ ሐዋርያት በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ይብሉ አብ ይነግር በእንተ ወልዱ ከመ ወልዱ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘዋሕድ ሎቱ፤ ወወልድ ይነግር ከመ እግዚአብሔር አብ ዘወለዶ ፤ ወመንፈስ ቅዱስ ይዜኑ ዘከመ ወፅአ እምአብ ወዘ ከመ ነሥአ እም ወልድ፤	፵፩፤ እኛስ የአብንና የወልድን የመንፈስ ቅዱስንም ነገር እናስተውል፤ ሐዋርያት እንዳስተማሩን ለርሱ አንድ የሚሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ልጁ እንደሆነ አብ የልጁን ነገር ይናገራል ብሎው፤ ወልድም የወለደው እግዚአብሔር አብ እንደ ሆነ ይናገራል፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ እንደወጣ (እንደ ሠረፀ) ከወልድም እንደ ነሣ ይናገራል ፤	41. But let us receive what the apostles taught us about the Father, the Son and the Holy Spirit saying: The Father declares of his Son that he is Jesus Christ his only One: And the Son tells that God the Father begat him: And the Holy Spirit proclaims that he proceeds from the Father and took of the things of the Son.[7]
፵፪፤ አሐቲ ምክር (ክብር) ወአሐቲ ሥልጣን ወኀይል ዘኢይትከፈል፤ አልቦ አመክንዮ ወኢቡዓዴ ለኀበ ዚአሁ ህላዌ ወአልቦ ሕፀት ወተውሳክ ለኀበ ዚአሁ መለኮት፤	፵፪፤ አንዲት ምክር (ክብር) አንዲት ሥልጣን የማይ ለይ አንድ ኃይልም ነው፤ በባሕርዩ ዘንድ ምክንያት መለየትም የለም፤ በመ ለኮቱም ዘንድ ጕድለትና ጭማሪ የለም፤	42. It is one honour and one authority and one power which can not be divided. There is neither reasoning nor separation of his position. There is neither subtraction nor addition in his divinity.
፵፫፤ በከመ አውሥአ እግዚ እነ ለአርዳኢሁ በእንተ ህላዌሆሙ እንዘ ይብል አልብነ ቀዳማዊ ወአልብነ ደኃራዊ አልብነ የማን ወአልብነ ፀጋም አልብነ ጠፈር ወአልብነ መሠረት ንሕነ ጠፈር ወንሕነ መሠረት፤	፵፫፤ ጌታችን ለደቀ መዛሙ ርቱ ያነዋወራቸውን ነገር እንደ ነገራቸው፤ ተቀዳ ሚና ተከታይ ቀኝና ግራ የለብንም ብሎ ፤ ጠፈር የለብንም መሠረትም የለብንም ጠፈርም መሠ ረትም እኛ ነን ፤	43. As our Lord answered his disciples about their nature saying, we have neither first nor last, we have neither right nor left, we have neither firmament nor foundation, we are the firmament and we are the foundation.

[7] John 16:15.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፵፬፤ አልቦ ዘይክል ርእዮተነ ወአልቦ ዘየአምር ዘከመ እፎ ህላዌነ፤ ንሕነ ነአምሮ ለኵሉ ወንሕነ ንጤይቆ ለኵሉ ናአትቶ ለልጹቅ ወናቁርቦ ለር ሑቅ፤ ንጸመም አው ያተ ልሳን ከመ ዘኢይ ሰምዕ፤ ወነአምር ለኖሳስ ልብ ዘውስጥ፤	፵፬፤ እኛን ማየት የሚቻለው የለም፤ አነዋወራችንም እንደምን እንደ ሆነ የሚያውቅ የለም፤ እኛ ሁሉን እናውቀዋለን ፤ ሁሉንም እኛ እንረዳ ዋለን፤ የቀረበውን እና ርቀዋለን የራቀውንም እናቀርበዋለን ፤ እንደ ማይሰማ ያንደበትን ጩኸት ቸል እንላለን፤ የውስጣዊን ልብ ለኖሳስ (ሹክሽክታ) እናውቃለን፤	44. None can see us and none can know how we live. We know all and we understand all, we make remote that which is near and bring nigh that which is afar off. We ignore the noise of the tongue as one who does not hear.[8] We know the whisper of the heart within.
፵፭፤ አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ደዴ ወአንቀጽ ወማኅደር፤	፵፭፤ አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም ደጅ በርና ማደሪያ ነን፤	45. My Father and I and the Holy Spirit are the gate, the door and the dwelling place.
፵፮፤ አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ግርማ ወጸጋ ወሞገስ፤	፵፮፤ አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም ግርማና ጸጋ ሞገስም ነን፤	46. My Father and I and the Holy Spirit are might, grace and favour.
፵፯፤ አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ፀሐይ ወብርሃን ወዋዕይ፤	፵፯፤ አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም ፀሐይና ብርሃን ዋዕይም ነን ፤	47. My Father and I and the Holy Spirit are sun, light and heat.
፵፰፤ አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ እሳት ወነበልባል ወፍሕም፤	፵፰፤ አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም እሳትና ነበል ባል ፍሕምም ነን ፤	48. My Father and I and the Holy Spirit are fire, flame and the burning coal.
፵፱፤ ከመዝ ህላዌነ ወከመዝ ፍጻሜነ ውመዋዕሊነ ኢኮነ ለዓለም አላ ለዓለም ወለ ዓለመ ዓለም፤ ዓዲ አልቦ ጕልቍ ወኢተፍጻሜት፤	፵፱፤ አነዋወራችን እንዲህ ነው ፍጻሜያችንም እንዲህ ነው፤ ዘመናችንም ለዓለም አይደለም ለዘለዓለም ዓለም ነው እንጂ፤ ዳግመኛ ቍጥርና ፍጻሜ የለውም፤	49. Such is our existence, such is our perfection, and our days are not finite but they endure forever. Again there is neither measurement nor end (of them).
፶፤ ይ. ዲ. ላዕለ ይኩን ሕሊናክሙ፤ በሰማይ የሃሉ ልብክሙ፤ አእምሩ ኀበ ዘትቀውሙ።	፶፤ ይ.ዲ. አሳባችሁ ወደ ላይ ይሁን፤ ልቡናችሁ በሰማይ ይኑር፤ የምትቆሙበትን ዕወቁ ።	50. *Deacon*: Let your thoughts be above. Let your hearts be in heaven. Know where you stand.
* * *	* * *	* * *
፶፩፤ ይ. ካ. ርጉቀ መዓት ወብዙኃ ምሕረት ወጻድቅ አልቦ አመ ተዐገሠ ወአልቦ አመ ኢተዐገሠ፤ ይትዔገሥ ለዘአበሰ እስከ ይገብእ ወይትመየጥ ኀቤሁ፤	፶፩፤ ይ.ካ. መዓቱ የራቀ ምሕ ረቱም የበዛ እውነተኛ፤ የታገሠበት ጊዜ የለም፤ ያልታገሠበትም ጊዜ የለም የበደለው ፈጽሞ ወደርሱ እስኪመለስ ድረስ ይታገ ሣል፤	51. *Priest*: He is slow to anger; His compassion is great, and He is righteous. There is no time when He is patient and another when He is impatient. He waits for the sinner until He comes back and returns to him.

[8] Isaiah 1:15.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፶፪ ፤ ወአመ ተምዐ ደምሰሰ ኃጥአነ በማየ አይኅ ፤ ወአትረፈ ሰማኒተ ነፍ ሳተ እለ ዐቀቡ ቃሎ ወምስለ አቡሆሙ ዐቀመ ኪዳነ ጽድቅ ዘለዓለም ፤ አምላከ አማልክት እሳት በላሚ ወእሳት ማሕየዊ ፤	፶፪ ፤ በተቈጣ ጊዜም ኃጥአንን በጥፋት ውኃ አጠፋ ፤ ቃሉን የጠበቁ ስምንት ሰዎችንም አተረፈ ፤ ከአባ ታቸውም ጋራ ለዘለዓለም የሚሆን የእውነት ኪዳንን አጸና (አቆመ) ፤ የአማል ክት አምላክ የሚያቃጥል እሳት የሚያድን እሳት ፤	52. When he was angry he destroyed the wicked with the flood and saved eight souls who kept His word, and He establish-ed with their father an everlasting covenant to righteousness. He is God of gods, consuming fire, and life-giving fire.
፶፫ ፤ መኑ ስሙ ወመኑ ስመ ወልዱ ዘከመ እፎ ብሔሩ ወዘከመ እፎ ሀገሩ ፤	፶፫ ፤ ስሙ ማነው? የልጁስ ስም ማነው? ብሔሩ እንደ ምን ያለ ነው? ሀገሩስ እንደምን ያለ ነው?	53. What is His name, and what is His Son's name?[9] Where is His dwelling-place and where is His country?
፶፬ ፤ መንበሩ በእሳት ክሉል ወማኅደሩ በማይ ጥፉር ወዲበ ተድባበ ቤቱ ሕን ባበ ማይ ዘኢይትከዐው ፤ ወእመንበሩ ይወፅእ ፀዓዕ ከመ ርስነ እሳት ውስጡ ብርሃን ዐቢይ ውስቴቱ ከመ ቀስተ ደመና ዘክረ ምት መብረቅ ዐውዱ ፤	፶፬ ፤ ዙፋኑ በእሳት የተከበበ ነው ፤ ማደሪያውም በውኃ የተታታ ነው ፤ በቤቱም ዙሪያ ላይ የማይፈስ የውኃ መርገፍ አለ ፤ ከዙፋኑም ብልጭልጭታ ይወጣል ፤ ውስጡ እንደ ጋለ እሳት ነው ፤ በውስጡ እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ያለ ደገኛ ብርሃን አለ ፤ ዙሪያው መብረቅ ነው ፤	54. His throne is compassed by fire and His abode is enveloped by water, and round the roof of His house hangs drops of water which do not fall. Flashes of light go out from his throne; within it is like blazing fire; in it there is great light like the winter rainbow; round it there is lightening.
፶፭ ፤ ወእምገበዋቲሁ ለውእቱ መንበር ፬ቱ እንስሳ (ከመ) እንዘ ይፀውሩ መልዕልተ ርእሶሙ መን በረ ስፉሐ ዘጎብረ በረድ ፀዓዳ ፤	፶፭ ፤ ከዚያም መንበር አጠገብ አራቱ እንስሳ ጎብሩ እንደ በረድ ነጭ የሆነ ሰፊ መንበር በራሳቸው እንደ ተሸከሙ ሆነው አሉ ፤	55. At the sides of the throne there are four creatures as if they carry on their heads the large throne which is like the white show.
፶፮ ፤ ወእምዐውዱ ለውእቱ መንበር ፳ወ፬ቱ ካህናተ ሰማይ ወቅድሜሆሙ ይሬእዩ ሥዕለ በግዑ ወልብሰ ዘንዝጎት በደም ወመጽሐፈ ጎቱመ ፤	፶፮ ፤ በዚህም መንበር ዙሪያ ሃያ አራት ካህናተ ሰማይ አሉ ፤ በፊታቸውም የበ ጉን ሥዕል ደምን የተረ ጨች ልብስንም የታተመ መጽሐፍንም ያያሉ ፤	56. Round about that throne there are twenty four heavenly priests;[10] in front of them they see the likeness of the lamb, the vesture dipped in blood,[11] and the sealed book.
፶፯ ፤ ወለለያድም ለውእቱ መንበር ይሰግዱ ፫ተ ጊዜ ለውእቱ ሥዕለ በግዑ ወለይእቲ ልብስ ዘንዝጎት በደም ወለ መጽሐፍ ጎቱም ወጢሰ ስብሐት ይመልዕ ውስተ ደብተራ መርጡል ወእ ምታሕቴሁ ለውእቱ መንበር ይነቅዕ ባሕር ዘ፪ኤ ፍናዊሁ ባሕር ዘብርሃን ወባሕር ዘነ ፋስ ፤	፶፯ ፤ ይህንም መንበር በዞሩ ቊጥር ለዚያ ለበጉ ሥዕልና በደም ለታለሸች ለዚያች ልብስ ለታተ መው መጽሐፍም ፫ ጊዜ ይሰግዳሉ ፤ በአዳራ ሹም ድንኳን የምስጋና ጢስ ይመላል ፤ ከዚህም መንበር በታች ጎዳናው ሁለት የሆነ ባሕር ይፈልቃል ፤ የብርሃን ባሕርና የነፋስ ባሕር ፤	57. Every time they go round that throne they prostrate themselves thrice before the likeness of the Lamb, the vesture dipped in blood and the sealed book. The smoke of glory fills the pavilion. From beneath that throne springs the sea of two courses, the sea of light and the sea of wind.

[9] Prov. 30:4.
[10] Rev. 4:4.
[11] Rev. 19:13

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፶፰ አኮ ህየ ዘይሄሉ አምላከ አማልክት ወአኮ ህየ ዘይትጋባእ እግዚአ አጋዕዝት ይሄሉ በአፍኣ ወይ ትረክብ በውስጥ ።	፶፰ የአማልክት አምላክ በዚያ የሚኖር አይደለም፣ የአ ጋዕዝትም ጌታ በዚያ የሚወሰን አይደለም፣ በውጭ ይኖራል በውስ ጥም ይገኛል ።	58. The God of gods does not live there; the Lord of lords is not limited therein, but He both lives without and is found within.
፶፱ ኢየሐውሩ ከመ ይርከ ብም ወኢይትጎጣእ ሶበ የኀሥሥም፣ ኢይትጎሠሥ ሶበ ይእኀዝም እስመ ብዑድ ውእቱ እምሕሊና ።	፶፱ ያገኙት ዘንድ አይሄዱም፣ በሹትም (በፈለጉትም) ጊዜ አይታጣም፣ በያዙት ጊዜ አይዳሰስም፣ ከሕሊና ልዩ ነውና ።	59. They do not go to find Him, and He is not absent when they seek Him. He is not felt when they take hold of Him because He is far above thought.
፷ የዐቅብ ባዕለ ወምስለ ነዳይ ይሄሉ ያፈቅር ትሑተ ወይትሔየይ ዕቡየ፣ ያጸድቅ ለእመ ፈቀደ ወያድኅን ለእመ ሠምረ ይጸመም ከመ ዘኢይሰምዕ ያረምም ከመ ዘኢይሬኢ፣ ይትዔገሥ ከመ ዘኢየአምር ያጕነዲ ከመ ዘኢይሁብ ።	፷ ባለጸጋውን ይጠብቃል፣ ከድሀም ጋራ ይኖራል፣ ትሑቱን ሰው ይወዳል፣ ትዕቢተኛን ግን ቸል ይላል፣ ቢፈቅድ ያጸድ ቃል ቢወድም ያድናል፣ እንደማይሰማ ቸል ይላል፣ እንደማያይ ዝም ይላል፣ እንደማያውቅ ይታገሣል፣ እንደማይሰጥ ያዘገያል ።	60. He keeps the rich; lives with the poor; loves the humble, and neglects the haughty. He will justify when He likes; will save when He is pleased; He disregards as if He does not hear; He keeps silent as if he does not see; He waits as if He does not know; He delays as if He does not wish to grant.
፷፩ አምላከ አማልክት ወእግ ዚአ አጋዕዝት እግዚአሙ ለአዚዛን ዘሎቱ ይሰግዱ መላእክት ወሊቃነ መላ እክት ።	፷፩ የአማልክት አምላክ የአ ጋዕዝትም ጌታ የጽኑ ዓን ጌታቸው መላእክትና ሊቃነ መላእክት የሚሰግ ዱለት እርሱ ነው ።	61. He is the God of gods, the Lord of lords, the Lord of the strong, before whom the angels and archangels prostrate themselves.
፷፪ አኮ ዘይሰግዱ ሎቱ በነ ጽሮ አላ ለመንበሩ ይሰ ግዱ ወለዕበዩ ይገንዩ፣ ወይሠሩ ውስተ ትርብ ዕተ ዓለም ለገቢረ ኵሉ ፈቃዱ፣ ሱራፌል ወኪሩ ቤል ይጸርሑ ወይብሉ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል፣ አኮ በኃይለ ትዕቢት ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘሞተ በእንተ ፍቅረ ሰብእ ።	፷፪ በማየት የሚሰግዱለት አይደለም፣ ለመንበሩ ይሰግዳሉ፣ ለጌትነቱም ይገዛሉ እንጂ፣ ፈቃዱን ሁሉ ለመሥራት ወደ አራቱ ማዕዘን ዓለም ይወጣሉ፣ ሱራፌልና ኪሩቤል በትዕቢት ኃይል ያይደለ ጩኸው ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል የማይሞት ስለ ሰው ፍቅር የሞተ ቅዱስ ሕያው ይላሉ ።	62. They do not prostrate themselves before Him because they see Him, but they prostrate themselves before His throne and praise His greatness. They fly towards the four ends of the world to do all His will. Seraphim and Cherubim shout and say, yet without pride: Holy God, holy mighty, holy living, immortal, who yet died for the love of man.
፷፫ ወእምአሐቲ መዝገብ ዘእ ምእስትንፋሰ አፉሁ ይሠ ርዓ ወያሕመለምላ ነፍ ሳት እለ ይትወለዳ ውስተ ዓለም ።	፷፫ በዓለም የሚወለዱ ነፍሳት ከአፉ እስትንፋስ ከተገኘች ከአንዲት መዝገብ ይወ ጣሉ ይለመልማሉም ።	63. From the one treasury[12] formed from the breath of His mouth proceed and grow the souls who multiply in the world.

[12] i.e. Adam or one baptism.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፷፬። ወበአሐቲ መዝገብ ይት ወደይ ሥርናይ ዘአልቦ ክርዳድ፣ ህየ ይሠየማ ወህየ ይትዐቀባ ነፍሳቲ ሶሙ ለጻድቃን እስከ አመ ይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ።	፷፬። በአንዲትም መዝገብ ክርዳድ የሌለበት ስንዴ ይገባል፣ የጻድቃን ነፍሶቻቸው በዚያ ይኖራሉ፣ በዚያም ይጠበቃሉ፣ ለሁሉ እንደ ሥራው እስኪከፍለው ድረስ ።	64. In one treasury there will be gathered wheat without tares. There will be put and kept the souls of the righteous until all are rewarded according to their deeds.
፷፭። ህየ ሀሎ ፍሥሓ ወሐሜት፣ ህየ ሀሎ አዳም አበ ኵሉ ህየ ሀለዉ አቤል ወሴት ወኄኖስ አርእስተ አበው ምስለ ኵሉ ፍሬሆሙ።	፷፭። ከዚያ ፍሥሓ ሐሜትም አለ፣ የሁሉ አባት አዳም ከዚያ አለ፣ የአበው አር እስቶች አለቆች አቤልና ሴት ሄኖስም ከፍሬያቸው ጋራ በዚያ አሉ ።	65. There are pleasure and happiness. There is Adam the Father of all. There are Abel, Seth and Enoch the patriarchs together with all their seed.
፷፮። ህየ ሀለዉ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ዐርካነ እግዚእ፣ ህየ ሀለዉ ሙሴ ወአሮን ካህናት፣ ህየ ሀለዉ ዳዊት ወሕዝ ቅያስ ወኢዮስያስ ወኵ ሎሙ ርቱዓነ ሃይማኖት ነገሥት።	፷፮። የጌታ ወዳጆች አብርሃ ምና ይስሐቅ ያዕቆብም ከዚያ አሉ፣ ሙሴና አሮን ካህናት ከዚያ አሉ፣ ዳዊትና ሕዝቅያስ ኢዮስ ያስም፣ ሃይማኖታቸው የቀና ነገሥታትም ሁሉ።	66. There are Abraham, Isaac and Jacob, the beloved of the Lord. There are Moses and Aaron the priests. There are David, Hezekiah and Josiah and all the kings of a right faith.
፷፯። ህየ ሀለዉ ነቢያት ምስለ ትንቢቶሙ፣ ህየ ሀለዉ አርድእተ ዋሕድ ዘመራ ጉት ውስተ እደዊሆሙ እንዘ ይነብሩ አንቀጸ ከመ ያብኡ ውስቴታ ዘፈቀዱ።	፷፯። ነቢያት ከትንቢታቸው ጋራ ከዚያ አሉ ፣ መክ ፈቻዎች በእጆቻቸው የተያዙ የዋሕድ ደቀ መዛሙርት ከዚያ አሉ፣ በበር ተቀምጠው የወደ ዱትን ወደእርስዋ ያገቡ ዘንድ ።	67. There are the prophets with their prophecies, there are the disciples of the One, in whose hands are the keys, sitting at the door to take in whom they will.
፷፰። ህየ ሀለዉ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ወኤጲስቆጶሳት ቀሳ ውስት ወዲያቆናት እለ አዕለዉ ምግቦሙ ዘተአመ ኖሙ እግዚአሙ።	፷፰። የጳጳሳት አለቆች ጳጳሳ ትና ኤጲስቆጶሳት ቀሳው ስትና ዲያቆናት ጌታቸው ያመናቸው ሹመታቸውን የመለሱ ከዚያ አሉ ።	68. There are the patriarchs, archbishops, bishops, priests and deacons who gave full account of their stewardship which was entrusted unto them by their Lord.
፷፱። ህየ ሀለዉ ሰማዕት እንዘ ይበርቅ አክሊሎሙ ምስብ ዒተ እምፀሐይ፣ ህየህ ለዉ ጻድቃን በትዕግሥ ቶሙ።	፷፱። ሰማዕታት ዘውዳቸው ከፀሐይ ሰባት እጅ እያ በራ ከዚያ አሉ፣ ጻድቃን በትዕግሥታቸው ከዚያ አሉ ።	69. There are martyrs whose crowns shine seven times brighter than the sun. There are the righteous in their patience.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፸። ህየ ህለዉ ዕድ ወአንስት ትዕይንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እለ አልቦሙ ጕልቍ፤ ህየ ይነብሩ በትፍሥሕት ወበሐሤት እስከ አመ ይትሜጠዉ ርስቶሙ ምክዕቢተ እምቀዳሚ።	፸። ቍጥር የሌላቸው የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም ሠራዊት ወንዶችም ሴቶችም ከዚያ አሉ ፤ በፍጹም ደስታ በሐሤትም ከዚያ ይኖራሉ፤ ከቀድሞው ይልቅ ዕፅፍ ርስታቸውን እስኪቀበሉ ድረስ ፤	70. There are men and women, the hosts of the Father, the Son and the Holy Spirit whose number cannot be known. They live there in pleasure and happiness till they receive twofold more than before.[13]
፸፩። ህየ ይነብሩ ጻድቃን በክብር የዋሃን በክብር ወጎሩያን በክብር፤ ንስ እለክ እግዚኦ ኪያክ መሠጥወ ኪያክ ሰማዔ ወኪያክ ረዳኤ፤	፸፩። ጻድቃን በክብር፤ የዋሃን በክብር የተመረጡትም በክብር ከዚያ ይኖራሉ፤ አቤቱ የምትመልስ አንተን፤ የምትሰማ አንተን፤ የምትረዳ አንተን እንለምንሃለን ፤	71. There live in honour the righteous, the meek and the elect. O Lord we offer our prayer unto you who does answer, who are the hearer and the helper.
፸፪። ናስተበቍዐከ እግዚኦ በእንተ እለ ኖሙ ወፈለሱ እምዝንቱ ዓለም ኃላፊ ወተሠልጠ ሥልጣነ ሞት ላዕሌሆሙ ወተከድኑ ታሕተ ክፈር።	፸፪። አቤቱ ከዚህ ከሚያልፍ ዓለም ተለይተው ስለ ሞቱና ስለተሰደዱ የሞት ሥልጣን ስለ ሠለጠነባ ቸውና ከመቃብር በታች ስለተከደኑ ሰዎች እንማ ልድሃለን ፤	72. We supplicate you, Lord, on behalf of those who have fallen asleep and departed from this corruptible world, and on behalf of those of whom the authority of death took hold, and of those who are covered within the grave.
፸፫። ንስእለከ እግዚኦ (ወናስ ተበቍዐከ) ከመ ትጸውዖሙ ውስተ ትንሣኤ ክብር እንዘ ታነሥእ ሥጋ አኅቢረከ ዘምስለ መንፈስ፤ ወእንዘ ተዐሲ ዕሴተ ሠናየ ዘዐይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢ ተሐለየ ዘአስተዳሉከ በወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም።	፸፫። አቤቱ ሥጋን ከመንፈስ ጋራ አንድ አድርገህ ስታስነሣ በክብር ወደ መነሣት ትጠራቸው ዘንድ እንለምንሃለን፤ እንማል ድሃለን፤ ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን በሰው ልቡናም ያልታሰበውን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ያዘጋጀኸውን በጎ ዋጋ እየሰጠህ ለዘለዓለሙ ፤	73. We pray you, Lord, and beseech you to call them to an honourable resurrection when you raise the body uniting it with the spirit, and when you give that good gift which eye has not seen, nor ear heard, neither has it entered into the heart of man, which you did prepare through your Son Jesus Christ, world without end.
፸፬። ይ. ዲ. በእንተ ብዑዕ ።	፸፬። ይ.ዲ. በእንተ ብዑዕ (ቅዳ. ሐዋ. ከቍ ፮-፱።)	74. *Deacon*: For the sake of the blessed ... (*Anaphora of the Apostle* No. 6-9)
፸፭። ይ. ካ. ንፍቅ ። ጸሎተ ቡራኬ።	፸፭። ይ.ካ. ንፍቅ ጸሎተ ቡራኬ (ቅዳ. ሐዋ.ከቍ ፲-፳፩።)	75. *Asst. Priest*: *Prayer of Benediction* (*Anaphora of the Apostles* No. 10-21).

[13] i.e. more than they get in paradise, the waiting place of the righteous.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፸፮፤ ይ. ዲ. ንፍቅ፣ መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሉሙ ሕዝበ ክርስቲያን።	፸፮፤ ይ.ዲ.ንፍቅ፣ አቤቱ የጳጳሳቱን አለቆች ጳጳሳቱንና ኤጲስቆጶሳቱን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን የክርስቲያንም ወገኖች ሁሉ ማራቸው ይቅርም በላቸው ።	76. *Asst. Deacon*: Lord, pity and have mercy upon the patriarchs, archbishops, bishops, priests, deacons and all the Christian people.
* * *	* * *	* * *
፸፯፤ ይ. ካ. እግዚአብሔር አብ ዘፈነወ ወልዶ ዋሕደ ከመ ይኅድር ውስተ ሥጋ ወለት እንተ ኢተ አምር ምተ ተዐቍረ ውስተ ማኅፀን ሠዓሌ ሕፃናት እንዘ ኢይትጋባእ ተሰብአ እንዘ አምላክ ውእቱ ወተወልደ እንዘ እሳተ መለኮት ውእቱ ተሐፅነ አኮ በትርሲት ወክብር፤ አላ ከመ ውሉደ ነዳያን ልህቀ በዐቢይ ተግሣጽ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ	፸፯፤ ይካ. እግዚአብሔር አብ አንድ ልጁን የሰደደው ወንድ በማታውቅ (በወለት) በድንግል ሥጋ ያድር ዘንድ ነው፣ ሕፃናትን የሚፈጥር እርሱ ሳይወሰን በማኅፀን ተወሰነ ፣ አምላክ ሲሆን ሰው ሆነ፣ እሳተ መለኮትም ሲሆን ተወለደ ፣ አደገ በጌጥና በክብር አይደለም፣ እንደ ድሆች ልጆች ለዘመዶቹ እየታዘዘ በብዙ ተግሣጽ አደገ እንጂ ፣	77. *Priest*: God the Father sent his only-begotten Son to abide in the body of a daughter who did not know a husband; and the creator of infants was kept in the womb without being limited; He was made man while He was God, and was born while He was the fire of the godhead, and grew without adornments or honour, but grew like the children of the poor, chastened greatly and obeying his relatives.
፸፰፤ አድነነ ርእሶ ከመ ያጥምቆ ገብር እንዘ ንጹሕ ውእቱ እምኃጢአት፣ ገብረ ተአምራተ እስከ ረሰየ ማየ ወይነ ወእስከ አጽገበ አእላፈ ብዙኃነ በገዳም፤	፸፰፤ ከኃጢአት ንጹሕ ሲሆን አገልጋዩ ያጠምቀው ዘንድ ራሱን አዘነበለ፣ ውኃን ጠጅ እስከማ ድረግ ድረስ ተአምራት አደረገ፣ በምድረ በዳም ለብዙ ሰዎች እስኪ ያጠግብ ድረስ፤	78. He bowed his head to be baptized by a servant though He was pure from sin. He did miracles changing water into wine and satisfying many thousands in tbe wilderness.
፸፱፤ በዝየ ዕርገተ ዕጣን ፣ ይ. ሕ. ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ፫ተ ጊዜ።	፸፱፤ በዚህ ጊዜ ዕጣኑን ያሳርግ (ቅዳ. ሐዋ. ቍ ፴፫፤) ይ.ሕ. አቤቱ በመንግሥትህ አስበን ፫ ጊዜ ፤ (ቅዳ. ሐዋ. ቍ ፴፬፤)	79. *At this time he shall cense.* *People*: Remember us, Lord, in your kingdom. (*to be repeated thrice, Anaphora of the Apostle* No. 34).
* * *	* * *	* * *
፹፤ ይ. ካ. አ ዘአሜሃ ትውልድ ያራ አዕይንቲሆሙ ከመ ኢይርአይዎ ደንቀዋ እዘኒ ሆሙ ከመ ኢይስምዕ ዕዎ፣ ወተጸለለ ልቦሙ ከመ ኢያእምርዎ አምሰልዎ ሰብአ ለዘየኅድግ ኃጢአተ ወኰነንዎ ለመ ኰንነ መኳንንት	፹፤ ይ.ካ. ወዮ በዚያ ጊዜ የነበሩ ትውልድ እንዳ ያዩት ዓይናቸው ታወረ፣ እንዳይሰሙት ጆሮዋቸው ደነቆረ፣ እንዳያውቁትም ልቡናቸው ተሸፈነ ፣ ኃጢአትን ይቅር የሚለውን እርሱን ዕሩቅ ብእሲ ሲን አስመሰሉት፣ በመኳንንት ላይ የሚፈርደውን ፈረዱበት ፤	80. *Priest*: O! the eyes of that generation were blinded so that they might not see Him, and their ears were made deaf so that they might not listen to Him, and their hearts were closed so that they might not know Him, they claimed Him who forgives sin to be a mere man, and judged the judge of judges.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፹፩፤ ወኀረየ እምውስቴቶሙ ፲ወ፪ቱ ሐዋርያተ ወአንሶሰወ ምስሌሆሙ ወአርአዮሙ ሥርዓተ ምሥጢር ዘቍርባን፤	፹፩፤ ከእነሱም ወገን አሥራ ሁለት ሐዋርያትን መረጠ፤ ከነርሱም ጋራ ተመላለሰ፤ የቍርባን ምሥጢረ ሥርዓትንም አሳያቸው ፤	81. He chose twelve apostles from among them, walked with them and showed them the mysterious order of the holy communion.
፹፪፤ ይ. ዲ. አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት፤	፹፪፤ ይ.ዲ. ቀሳውስት እጆቻችሁን አንሡ ፤	82. *Deacon*: Priests, raise up your hands.
፹፫፤ ይ. ካ. ነሥአ ኅብስተ በቅድሜሆሙ፤ በዝየ ያንሥእ ኅብስተ፤	፹፫፤ ይ.ካ. በፊታቸው ኅብስትን አንሥቶ ያዘ፤ በዚህ ጊዜ ኅብስቱን ያንሣ፤	83. *Priest*: He took bread before them. *At this time he shall raise the bread.*
፹፬፤ ይ. ሕ. ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን፤	፹፬፤ ይ.ሕ. እናምናለን ፤ ይህ እርሱ እንደ ሆነ በእውነት እናምናለን ፤	84. *People*: We believe that this is He; truly we believe.
፹፭፤ ይ. ካ. ባረከ ፤ ቡራኬ ፫ተ ጊዜ ፤ ወእምዝ ያንቅዖ ለኅብስት ኅበ ፭ ገጽ ንስቲተ እንዘ ኢይሌልዮ፤ ወይቤ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት <<እማሬ>> ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትወሀብ ለኅድገተ ኃጢአት፤	፹፭፤ ይ.ካ. ባረከ ፤ ሦስት ጊዜ ይባርክ፤ ከዚያም በኋላ ኅብስቱን ሳይለየው ከአምስት ላይ ጥቂት ያንቃው፤ ይህ ኅብስት ‹‹እማሬ›› ለኃጢአት ማስተሥረያ ስለ ናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው ንሡ ብሉ አለ ፤	85. *Priest*: blessed, (*benediction three times, then he shall indent the Host lightly with his thumb in five places without separation*), and said, Take, eat, this (*pointing*) bread is my body which will be given on your behalf for the remission of sin.
፹፮፤ ይ. ሕ. አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንት አመን ንሴብሐከ አ እግዚእነ ወአምላክነ ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን ፤	፹፮፤ ይ.ሕ. አሜን አሜን አሜን እናምናለን እንታ መንማለን፤ ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤ እና መሰግንሃለን፤ ይህ እርሱ እንደሆነ በእውነት እና ምናለን፤	86. *People*: Amen amen amen, we believe and confess, we glorify you, O our Lord and our God; that this is he we truly believe.
፹፯፤ ይ. ካ. ወከማሁ ጽዋዐኒ ባረከ (ወቀደሰ)፤ ቡራኬ ፫ተ ጊዜ ፤ ወይቤ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ << እማሬ >> ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዐው ለኅድገተ ኃጢኣት፤ ወይነክንኩ ለጽዋዕ በትእምርተ መስቀል በእዴሁ ዘየማን፤ ይ. ሕ. አሜን አሜን አሜን፤	፹፯፤ ይ.ካ. እንዲሁም ጽዋውን ባረከ አከበረም ፤ ሦስት ጊዜ ይባርክ ፤ ይህ ጽዋ ‹‹እማሬ›› ለኃጢአት ማስተሥረያ ስለናንተ የሚፈስ ደሜ ነው፤ ንሡ ጠጡ አላቸው ፤ ጽዋውን በቀኝ እጁ በአራቱ ማዕዘን ይወዝውዘው፤ ይ.ሕ. አሜን አሜን አሜን ፤	87. *Priest*: And likewise also the cup: he blessed (*benediction three times*) and hallowed and said, Take, drink, this (*pointing*) cup is my; blood which will be shed on behalf of you for the remission of sin. *He shall then move the cup with his right hand in the sign of the cross.* *People*: Amen amen amen.
* * *	* * *	* * *

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፹፰፤ ይ. ካ. አሜሃ ኢየሱስ ይቤ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት ዘውእቱ መስተፍሥሒ ትኩዛን፤	፹፰፤ ይ.ካ. ያን ጊዜ ኢየሱስ ነፍሴ እስክ ሞት ደርሳ አዘነች አለ፤ ይኸውም ያዘኑትን ደስ የሚያሰኛ ቸው ነው፤	88. *Priest*: At that time Jesus said, My soul is exceedingly sorrowful, even unto death, the death which will make the sad rejoice.
፹፱፤ በይእቲ ሌሊት አኀዝዎ፤ ወጸቢሖ ረበናተ አይሁድ ወሊቃነ ካህናት ምስለ ጲላጦስ መስፍን ወነበሩ ዐውደ ለኰንኖቱ፤	፹፱፤ በዚያች ሌሊት ያዙት፤ በነጋም ጊዜ የአይሁድ መምህሮችና የካህናት አለቆች ከገዢ ከጲላጦስ ጋራ ሊፈርዱበት በአደባ ባይ ተቀመጡ ፤	89. In that night they took hold of Him, and when it was day the masters of the Jews and the chief priests sat with Pilate, the ruler, in the court for his judgement.
፺፤ አሠርዎ ድኅሪተ ከመሰ ራቂ ወተለምሙ በፍቅር ከመ በግዕ የዋህ ወነበሩ ዐውደ ለኰንኖቱ አቀ ምዎ ቅድሜሆሙ ለዘ ሎቱ ይቀውሙ ሠራዊተ መላእክት በፍርሀት ወበ ረዓድ፤	፺፤ እንደ ሌባ የኋሊት አሠ ሩት፤ እንደ የዋህ በግ በፍቅር ተከተላቸው፤ ሊፈርዱበት በአደባባይ ተቀመጡ፤ የመላእክት ሠራዊት በመፍራት በመንቀጥቀጥ የሚቆሙ ለትን በፊታቸው አቆ ሙት፤	90. They shackled Him with His hands behind Him like a thief, and He followed them in love like a meek sheep. They sat at the court to judge Him. They made Him to stand before them, Him before whom the hosts of angels stand in fear and trembling.
፺፩፤ ገብር እኩይ አጽንዐ እዴሁ ከመ ይጽፍዖ ገጸ ለዘኢአበሰ፤ ሎቱ ያደንኑ ሎቱ ከመ ይስግዱ በትዕ ቢት ለዘሎቱ ይሰግዱ ሊቃነ መላእክት በዐቢይ ድንጋፄ፤	፺፩፤ ክፉ ባሪያ እርሱን ያልበደ ለውን ይጸፋው ዘንድ እጁን አጸና፤ የመላእክት አለቆች በፍጹም ድንጋፄ ለሚሰግዱለት ለርሱ በትዕቢት ይሰግዱ ዘንድ አጐነበሱለት፤	91. An evil servant strengthened His hand to strike the innocent One; they howed with haughtiness before Him to whom the archangels bow in great trembling.
፺፪፤ አስተቀጸልዎ አክሊለ ዘሦክ ለርእሰ ሕይወት ሰለብዎ አልባሲሁ ወአ ልበስዎ ከለሜዳ ዘለይ ለዘይትዐጸፍ ብርሃነ ከመ ልብስ፤	፺፪፤ የሕይወትን ራስ የሾህ ዘውድ ደፉበት፤ ብርሃንን እንደ ልብስ የሚጐናጸፈ ውን ልብሱን ገፈው ቀይ ግምጃ አለበሱት ፤	92. They crowned the Head of life with a crown of thorns, stripping Him they clothed Him, who is dressed in light like a garment, with a scarlet rohe.[14]
፺፫፤ ወወሰድዎ ኀበ ይሰቅ ልዎ ብሔረ ዘስሙ ቀራንዮ አያርዎ መስ ቀሎ ወደክመ ኢየሱስ በፀዊረ መስቀሉ ወሐ ፈወ እስመ ክቡድ ውእቱ	፺፫፤ ወደሚሰቅሉበት ስሙ ቀራንዮ ወደሚባል ቦታ ወሰዱት፤ መስቀሉን አሸ ከሙት፤ ኢየሱስም መስ ቀሉን በመሸከም ደከመ ወዛ፤ ከባድ ነውና፤	93. They took him to the place of crucifixion called Calvary, burdening Him with his cross, so that Jesus was wearied in the carrying of his cross and sweated because it was heavy.
፺፬፤ ኰለቍዎ ምስለ ፈያት ወአዕረግዎ ዲበ ዕፅ ወሰቀልዎ ዘአልቦ ምሕ ረት በከመ ሕጎሙ፤	፺፬፤ ከወንበዴዎች ጋራ ቈጠ ሩት፤ ወደ እንጨትም አውጥተው ምሕረት የሌለው ስቅለትን እንደ ሕጋቸው ሰቀሉት ፤	94. They numbered Him among the thieves, raised Him upon the cross, and crucified Him, without mercy, according to their law.

[14] See the Anaphora of St. John Chrysostom 47:50.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፺፭፤ ኦ አእዳው እለ ለሐኪሁ ለአዳም ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል ፤ ኦ አእጋር እለ አንሶሰዋ ውስተ ገነት ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል፤	፺፭፤ አዳምን የፈጠሩ እጆች ወዮ በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፤ በገነት የተመላለሱ እግሮች ወዮ በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ ፤	95. Oh! the hands which formed Adam were nailed on the cross. Oh! the feet which walked in paradise were nailed on the cross.
፺፮፤ ኦ አፍ ዘነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈሰ ሕይወት ሰረበ ብሒዐ ወሕርቤ ቱሱሐ ዘምስለ ሐሞት፤	፺፮፤ በአዳም ፊት የሕይወትን መንፈስ እፍ ያለ አፍ ወዮ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ መጣጣንና ከር ቤን ጠጣ ፤	96. Oh! the mouth which breathed the breathe of life into the face of Adam drank vinegar and myrrh mixed with gall.
፺፯፤ ገዐረ ኢየሱስ በሕማሙ ወጸርሐ ኀበ አቡሁ አድነነ ርእሶ ወወፅአት መንፈሱ ሶቤሃ፤	፺፯፤ ኢየሱስ በሕማሙ (በመከራው) አሰምቶ ጮኸ፤ ወደ አባቱ ጮኸ፤ ራሱን ዘለለ አደረገ ፤ ያን ጊዜ ነፍሱ ወጣች (ተለየች) ፤	97. Jesus groaned in his suffering, cried to his Father, bowed his head and gave up his spirit.
፺፰፤ ረገዝዎ ገቦሁ በኵናት ጸሊም በዘሎቱ አንሐቡ፤ አውረድዎ እምዕፅ ወወደይዎ ውስተ መቃብር አኮ ኀበ መቃብረ ዚአሆሙ ዘወደይዎ አላ አፍአ ኀበ መቃብረ እንግዳ ዘቦቱ እመቱ ወጎተ ምዎ በእብን፤	፺፰፤ ለእርሱ ብለው ባሠሩት በጥቁር ጦር ጐኑን ወጉት፤ ከእንጨት አውርደው በመቃብር አኖሩት፤ በነርሱ መቃብር ያኖሩት አይደለም፤ ከከተማ ውጭ ሦስት ክንድ በሚሆን በስደተኛ መቃብር ነው እንጂ በደንጊያም ገጠሙት ፤	98. They pierced him in his side with a black spear which they prepared for Him; took Him down from the tree, and buried Him in the grave. They did not put Him in their own grave, but outside in a stranger's grave of three cubits, and closed it with a stone.
፺፱፤ ወእንዘ ሀሎ ህየ ጸርሐ ኀበ አዳም ገብሩ ወኀበ ኵሎሙ ደቂቁ።	፺፱፤ በዚያም ሳለ ወደ አገልጋዩ ወደ አዳም ወደ ልጆቹም ሁሉ ጮኸ ።	99. While He was there He cried towards Adam, his servant, and all his children.
	* * *	
፻፤ ይ. ካ. እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ፤ ይ. ሕ. ምስለ መንፈስክ፤ ይ. ካ. አእኵትዎ ለአምላክነ፤ ይ. ሕ. ርቱዕ ይደሉ ፤ ይ. ካ. አልዕሉ አልባቢክሙ ፤ ይ. ሕ. ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ፤ አቡነ ዘበሰማያት ፤ ፫ተ ጊዜ፤ አንተ ውእቱ እግዚእነ ወአምላክነ፤	፻፤ ይ.ካ. እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን ፤ ይ.ሕ. ከመንፈስህ ጋራ፤ ይ.ካ. አምላካችንን አመስግኑት ፤ ይ.ሕ. እውነት ነው ይገባል፤ ይ.ካ. ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ፤ ይ.ሕ. በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን የሰማይ አባታችን ሆይ፤ ፫ ጊዜ ጌታችንና አምላካችን አንተ ነህ ፤	100. *Priest*: The Lord be with you all. *People*: And with your spirit. *Priest*: You give thanks unto our God. *People*: It is right, it is just. *Priest*: Lift up your hearts. *People*: We have lifted them up unto the Lord our God. Our Father who are in heaven. (*to be repeated thrice*). You are our Lord and our God.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፻፩፤ ይ. ካ. ወሶበ ይቤ ዘንተ ለአዳም ገብሩ ተፈሥሐ አዳም ወወፅአ ምስለ ኵሎሙ ደቂቁ ወቦአ ውስተ ሀገር ቅድስት በከመ ተብህለ፤	፻፩፤ ይ.ካ. ይህንን ለአገልጋዩ ለአዳም በተናገረ ጊዜ አዳም ደስ አለው ፣ ከል ጆቹ ሁሉ ጋራ ወጥቶ ወደ ቅድስት አገር ገባ ፣ እንደ ተነገረ፤	101. *Priest*: When he said this to Adam, his servant, Adam rejoiced, went out with all his children and entered into the holy city, as it was said.
፻፪፤ ወካዕበ ከመ ያርኢ ስብሐተ ትንሣኤሁ አሥረቀ ንስቲተ መለኮቶ ወአውደቆሙ ለአለ የዐቅቡ ዝኆሮ፤	፻፪፤ ዳግመኛም የትንሣኤውን ክብር ይገልጽ ዘንድ ጥቂት ብርሃኑን አወጣ፣ መቃብ ሩን የሚጠብቁትንም ጣላ ቸው፤	102. And also, to reveal the glory of his resurrection, He revealed a little of His Divinity[15] and caused those who were watching His grave fall down.
፻፫፤ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት በዕለት ጥይቅት ቦአ ኀበ ሀለዉ አርዳኢሁ ወአርአዮሙ ርግዘተ ገቦሁ ወቅንዋተ እደዊሁ ወእገሪሁ፤ ወነበረ ምስሌ ሆሙ እንዘ ይሜህሮሙ በእንተ መንግሥተ ሰማ ያት፤	፻፫፤ በሦስተኛዪቱ ቀን ተነሣ፣ በተረጋገጠች ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ገብቶ የጐኑን መወጋት የእጆቹን መቸንከር አሳ ያቸው፤ የመንግሥተ ሰማ ያትን ነገር እያስተማ ራቸው ከነርሱ ጋራ ኖረ፤	103. And He rose on the third day, and on the day which He had made known entered where His disciples were and showed them His pierced side and His nailmarked hands. He stayed with them teaching them concerning the kingdom of heaven.
፻፬፤ ወበ፵ ዕለት ዐርገ ሰማ ያተ ኀበ አብ ዘፈነዎ፣ ወካ ዕበ ይመጽእ አኮ ዘይመጽእ በትሕትና፣ አላ በስብሐተ አብ ዘወ ለዶ በመፍርሀ ሥልጣን ምስለ መላእክቲሁ ቅዱ ሳን በደመና ሰማይ ፤	፻፬፤ በአርባኛውም ቀን ወደ ላከው አብ ወደ ሰማይ ዐረገ፣ ዳግመኛም ይመ ጣል በትሕትና የሚ መጣ አይደለም በወለ ደው በአብ ጌትነት በሚያ ስፈራ ሥልጣን ከቅዱ ሳን መላእክቶቹ ጋራ በሰማይ ደመና ነው እንጂ ፤	104. On the fortieth day He ascended unto heaven to His Father who sent Him. Again He will come. He will not come in lowliness but in the glory of the Father, who begat Him, in fearful authority with His holy angels in the clouds of heaven.
፻፭፤ ይ. ሕ. ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድ ስተ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ ንሴ ብሐከ ወንትአመነከ ንስ እለከ ወናስተበቍዐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ፤	፻፭፤ ይ.ሕ. አቤቱ ሞትህን ቅድስት ትንሣኤህንም እንናገራለን ፣ ዕርገት ህን ዳግመኛም መምጣ ትህን እናምናለን ፣ እናመሰግንሃለን እናምን ሃለንም ፣ ጌታችንና አምላካችን ሆይ፣ እንለ ምንሃለን እንማልድሃ ለንም ፤	105. *People*: We proclaim your death, Lord, and your holy resurrection; we believe in your ascension and your second advent. We glorify you and confess you, we offer our prayer unto you and supplicate you, O our Lord and our God.
፻፮፤ ይ. ካ. ለትኩን እግዚኦ ምሕረትከ ላዕሌነ ወበ ከመ ላዕሌከ ተወከልነ፤	፻፮፤ ይ.ካ. አቤቱ ይቅርታህ ለኛ ትደረግልን፣ በአንተ እንዳመን መጠን ፤	106. *Priest*: Let your mercy, Lord, be upon us according as we hope in you.[16]
፻፯፤ ይ. ሕ. በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበ ሳነ፣ ፫ተ ጊዜ፤	፻፯፤ ይ.ሕ. አምላካችን ሆይ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይደ ለም፣ ፫ ጊዜ፤	107. *People*: According to your mercy, our God, and not according to our sins, (*to be repeated thrice*).

[15] Referring to the light which shone from the grave at the time of resurrection.
[16] Ps. 33:22.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፻፷፰፤ ይ. ካ. ወተጋብኦትነ ይኩን በከመ ተጋብኦቶሙ ለአርዳኢከ አንተ ዘእሙንቱ ወአንተ ዘለነ፤ አንተ ዘአሜሃ ወአንተ ዘይእዜ፤	፻፷፰፤ ይ.ካ. መሰብሰባችንም እንደ ደቀ መዛሙርትህ መሰብሰብ ይሁን፤ የነርሱ ፈጣሪ አንተ ነህ፤ የእኛም አንተ ነህ፤ ያን ጊዜ የነበርህ አንተ ነህ፤ ዛሬም ያለህ አንተ ነህ፤	108. *Priest*: Let our gathering be like the gathering of Your disciples; You are theirs and You are ours, You are the same then and You are the same now.
፻፷፱፤ ዚአከ ሰማያት ወዚአከ ምድር ዚአከ ጻድቃን ወዚአከ ኃጥኣን፤ እስመ አንተ ትትዐዶ አእላፈ ኃጢአት፤ ወታቀውም ውኁደ ተክለ ጽድቅ ወትፈቅድ ምክንያተ ለድኀንነ፤	፻፷፱፤ ሰማያት ያንተ ናቸው ምድርም ያንተ ናት ፤ ጻድቃን ያንተ ናቸው ኃጥአንም ያንተ ናቸው፤ ብዙውን ኃጢአት ይቅር ትላለህና፤ ጥቂቱን ስለ ጽድቅ ታቆማለህ፤ ለማዳንም ምክንያት ትሻለህ፤	109. Yours is heaven and Yours is earth; Yours are the righteous and Yours are the unrighteous, because you did regard thousands of sins. You establish the little thing to be a plant of righteousness, and you did use any means to save.
፻፸፤ ይ. ዲ. በኵሉ ልብ ናስ ተብቊዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግ ወነ፤	፻፸፤ ይ.ዲ. በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንማልደው፤ ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት ይሰጠን ዘንድ ፤	110. *Deacon*: With all the heart let us beseech the Lord our God that he grant unto us the good communion of the Holy Spirit.
፻፸፩፤ ይ. ሕ. በከመ ሀሎ ህልው ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም፤	፻፸፩፤ ይ.ሕ. በፊት እንደ ነበረ ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጅ ይኖራል ፤	111. *People*: As it was, is and shall be unto generations of generations, world without end.
፻፸፪፤ በዝየ ይኅትም ሥጋ በደም ጠሚየ በአጽባዕቱ፤ ይ. ካ. ደሚረከ ተሀቦሙ ለኵሎሙ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ ይኩኖሙ ንጽሐ ለእለ ይነሥእም ወኅሩየ ለእለ ይትሜጠውም፤ ከመ በርእየቱ የዓይ ሥከ ኃጢአት ትትመላኅ አበሳ ወትደምሰስ ጌጋይ ወትንሐይ ነፍስ እም አበሳሃ ፍጹመ፤	፻፸፪፤ በዚህ ጊዜ በጣቱ ጠምቶ በሥጋው ደሙን ይቅባ፤ ይ.ካ. ከርሱ ለሚቀበሉ ሁሉ አንድ አድርገህ ስጣቸው፤ ለሚቀበሉት ንጽሕን ይሆናቸው ዘንድ፤ ለሚቀበሉትም መመረጫ ይሆናቸው ዘንድ፤ እርሱን በማየት የኃጢአት እሾህነት ይቃጠል ዘንድ አበሳ ትነቀል ዘንድ፤ በደልም ትጠፋ ዘንድ፤ ነፍስም ከበደልዋ ፈጽማ ታርፍ ዘንድ ፤	112. *At this time he shall dip his finger into the Blood and sign the Body.* *Priest*: Grant it together unto all them that take of it, that it may be unto them for purity and for choice unto them who receive of it, so that by its appearance the thorn of sin may be burnt, iniquity may be rooted out, wickedness may be destroyed and the soul may get perfect rest from her iniquity.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፪፻፲፫ ፤ ይትቀፈጽ ኖኀተ ብርሃን ወይትረኀው አናቅጸ ስብ ሐት ወይትፈኖ መንፈስከ ቅዱስ ወሕያው እመካን ዘሥውር ህላዌሁ ይረድ ወይምጻእ ፤ ወያንጸብርቅ ዲበ ዝንቱ <<እማሬ>> ኅብስት ወይኩን ሥጋ ክርስቶስ አምላክነ ፤ ቡራኬ ላዕለ ኅብስት ፩ ጊዜ ፤	፪፻፲፫ የብርሃን ደጅ ይገለጥ ፤ የብርሃን በርም ይከ ፈት ፤ ቅዱስና ሕያው የሚሆን መንፈስም ይላክ ፤ አኗኗሩ ከተሠወረ ቦታ ይውረድ ፤ ይም ጣም ፤ በዚህም ኅብስት ‹‹እማሬ›› ላይ ያብራ ፤ የአምላካችንን የክርስቶ ስን ሥጋ ይሁን ፤ በኅብስቱ ላይ ፩ ጊዜ ይባርክ ፤	113. Let the gate of light be opened, and let the doors of glory be unlocked,[17] and let the living Holy Spirit be sent, descend and come from the place where he is hidden, and shine on this (*pointing*) bread that it may be the body of Christ our God, (*benediction over the bread once*),
፪፻፲፬ ፤ ወይትወለጥ ጣዕሙ ለዝ ንቱ <<እማሬ>> ጽዋዕ ወይኩን ደመ ክርስቶስ አምላክነ ፤ ቡራኬ ላዕለ ጽዋዕ ፩ ጊዜ ዓዲ ላዕለ ፪ሆሙ ፩ ጊዜ ፤	፪፻፲፬ ፤ የዚህ ‹‹እማሬ›› የጽዋው ጣዕም ተለውጦ የአምላ ካችንን የክርስቶስን ደም ይሁን ፤ በጽዋው ላይ ፩ ጊዜ ይባርክ ዳግመኛ በ፪ቱም ላይ ፩ ጊዜ ይባርክ ፤	114. and that the nature of this (*pointing*) cup may be changed to become the blood of Christ our God. (*Benediction over the cup once, and once more over both*).
፪፻፲፭ ፤ ይ. ሕ. አሜን እግዚኦ መሐረነ እግዚኦ መሐከነ እግዚኦ ተሣሃለነ ፤	፪፻፲፭ ፤ ይ.ሕ. አሜን አቤቱ ማረን አቤቱ ራራልን አቤቱ ይቅር በለን ፤	115. *People*: Amen, Lord have pity upon us, Lord spare us, Lord have mercy upon us.
፪፻፲፮ ፤ ይ. ካ. ወምስለ ኵሉ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተ ክርስቲያን መሐ ሮሙ ወተሣሃልዎሙ ወፈ ድፋደሰ ለእለ ኀረዩ ንዴተ ዚአየ ለመልእክተ ዝንቱ ምሥጢር መሐሮሙ ወተሣሃ ሎሙ ለዓለመ ዓለም አሜን ፤	፪፻፲፮ ፤ ይ.ካ. ከሁሉ በላይ የም ትሆን ያንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የማኅበ ርዋን ፍጻሜ ማራቸው ፤ ይቅርም በላቸው ፤ ይል ቁንም ይሆነን ምሥጢር ለማገልገል የእኔን ንዴት የመረጡትን ማራቸው ፤ ይቅርም በላቸው ፤ ለዘለ ዓለሙ አሜን ፤	116. *People*: Have pity and mercy upon the one, holy and universal Church together with the entire congregation, and especially have pity and mercy upon those who chose me, the poor one, to minister this mystery, world without end. Amen.
* * *	* * *	* * *
፪፻፲፯ ፤ ይ. ካ. ሀበነ ንኅበር በዘ ዚአከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርስ ፎራ ከመ ብክ ንሕየው ዘለኵሉ ዓለም ወለዓለመ ዓለም ፤ ይ. ሕ. ከማሁ ፤	፪፻፲፯ ፤ ይ.ካ. የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ መሆንን ስጠን ፤ በዚህም ጽርስ ፎራ (በሥጋው በደሙ) አድነን ፤ ለዓለሙ ሁሉ በምትሆን በአንተ ለዘለ ዓለሙ ሕያዋን እንሆን ዘንድ ፤ ይ.ሕ. እንደርሱ ፤	117. *Priest*: Grant us to be united through your Holy Spirit, and heal us by this oblation that we may live in you forever. *People: The people shall repeat his words.*

[17] See "The Anaphora of St. Jacob of Serough" 53..

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፻፲፰፤ ይ. ካ. ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወይት ባረክ ስመ ስብሐቲሁ ለይኩን ለይኩን ቡሩክ ለይኩን፤ ይ. ሕ. ከማሁ፤	፻፲፰፤ ይ.ካ. የእግዚአብሔር ስም ምስጉን ነው፤ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውም ምስጉን ነው፤ የጌትነቱም ስም ይመስገን፤ ይሁን ይሁን የተመሰገነ ይሁን ፤ ይ.ሕ. እንደርሱ ፤	118. *Priest*: Blessed be the name of the Lord, and blessed be he that comes in the name of the Lord, and let the name of his glory be blessed. So be it, so be it, so be it blessed. *People: The people shall repeat his words.*
